**GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA**
**Office of the Deputy Mayor for Education**

**Abigail Smith**
**Deputy Mayor for Education**

ጥቅምት 28 ቀን 2013

ወድ የተማሪ ወላጅ/የህብረተሰብ ዓባል፣

የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ድልድል ፖሊሲዎች ሂደትን ሰፋ ባለ መልኩ ለመመልከት በማደረግ ጥረት የዲ.ሲ. የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ወሰን እና የተማሪዎችን ድልድል ሂደት ግምገማ እያካሄድን ነው። የዚህ ሂደት ዓላማ የቤተሰቦችን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ -የተብራራ፣ ትክክለኛ እና በሚፈልጉት አካባቢ ከፈተኛ ጥራት ያለውትምህርት ቤት የማግኘት አማራጭያለው
የትምህርት ቤት ምርጫእና የተማሪዎች ድልድል ፖሊሲዎች መገንባት ነው።

በተለይ፡

- የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለመግባት ቤተሰቦችና ትምህርት ቤቶች ያላቸውን መብቶችና ኃላፊነቶችን ለማብራራት፣
- በየክፍሎቹ ደረጃ ግልጽና የተጣራ መንገድ መኖሩን ለማረጋገጥ በህዝብ ትምህርት ቤቶች፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን የተማሪዎች ዝውውርን በተመለከተ ለማሳወቅ፣
- የህዝብ ትምህርት ቤቶች ወሰኖች ከህዝብ ትምህርት ቤቶች ህንጻዎች ዐቅም እና ከሚጠበቀው የተማሪዎች ቁጥር ጋር መመጣጠኑን ማረጋገጥ፣ እና
- በአጠቃላይ በህዝብ ትምህርት ቤቶች እና በቻርተር ትምህርት ቢቶች የተማሪዎች ድልድል እና የምርጫፖሊሲዎችን ለማገናኘት ያሉትን ዕድሎች ማጥናት።

ዲስትሪክቱ ከ1970 ጀምሮ አጠቃላይ የተማሪዎቹን ድልድል ፖሊሲዎች፣ የህዝብ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት መገኘትን ወሰንና የዝውውር ሂደቶችን ጨምሮ ግምገማ አላደረገም። እስከዚያ ድረስ የዲሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች ተከፍተውና ተዘግተዋል እንዲሁም የከተማው ህዝብም ተለውጧል።

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ወራቶች፣ ወስጥ የእኔ ቢሮ አሁን ያሉትን ፖሊሲዎች እና የአሠራር ተመክሮዎችን ይገመግማል፣ የሚያጋጥሙትን እክሎችን ይለያል፣ መረጃዎችን ይመረምራል፣ እንዲሁም መፍትሄዎችን ይሰጣል። በዚህ ጉዳይ እንዲረዳን፣ አማራጮቹን የሚገመግም እና መፍትሄዎች የሚሰጥ ህያ አንድ ዓባሎች ያካተተ ኮሚቴ መስርተናል። **የዲ.ሲ. የተማሪዎች ድልድል አማካሪ ኮሚቴ** የተለያዩ አስተያየቶች ያላቸውበህዝብ የትምህርት ዘዴዎችና በከተማችን የወደፊት ሁኔታ ላይ በቂ ልምድ ያላቸውዓባሎችን ያካትታል። የህዝብ ትምህርት ቤቶች ወላጆችን የሚያካትተው ኮሚቴ በግንቦት 2014 መቅረብ የሚችሉ ፍትሃዊ እዮታና ዕወቅና ያላቸውየህዝብ አስተያየቶችና ወይይቶችን ያቀርባል። ዕቅዱ በ2014 በበልግ ወራት ተፈጽሞ በ2015 በበልግ ወራት በሥራ ላይ ይወላል።

ህዝቡን በአማካሪ ኮሚቴ ብቻ ማሳተፍ በቂ አይደለም። ይህ ሂደት ሰፋ ያለ የህዝብ ተሳትፎና አስተዋፅዎ ከሌለበት የተሳካ ወጤት አይኖረወም። ልጆቻቸውን የህዝብ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ ቤተሰቦች እና በከተማዋ ማህበራዊና የኢኮኖሚደህንነት ተጠቃሚየ ሆኑ ነዋሪዎች የዲ.ሲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ድልድልን የሚያካትተውፖሊሲ ላይ ድርሻ አላቸው። ስለዚህ፣ በጠቅላላውሂደት ወላጆች እና የህብረተሰቡ አካሎች እንዲካፈሉ እና አስተዋፅዎ እንዲያደርጉ በርካታ ዕድሎች አዘጋጅተናል።

- **በጥናት ቡድኖች መካፈል**

- **የሥራ ቡድኖች ጋር ለመሥራት በፈቃድ መካፈል**
- **ሀሳብዎን እና አስተያየትዎን በድህረ ገጽ EngageDC.org ማካፈል**
- **ከተማአቀፍ ወይይቶች ወስጥ መካፈል**
- **በኢንተርኔት በሚደረጉ ጥናቶች መካፈል**

ለመሳተፍ እና እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ በበለጠ ለማወቅ እና ለሥራና ለጥናት ቡድኖች ለመካፈል ለመመዝገብ እባክዎ ከዚህ ጋር የተያያዘውን "አብዛኛውን ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች" ይመልከቱ ወይም በድህረ ገጽ dme.dc.gov ይጎብኙ"።

ከፊታችን ብዙ አስቸጋሪ ሥራዎች ተደቅነዋል፣ ይሁን እንጂ በአንድነት ለተማሪዎቻችን እና ለቤተቦች የተሻለውን እንደምናደረግ እርግጠኛ ነኝ።

አመሰግናለሁ፣



አቢጌል ስሚዝ
የትምህርት ክፍል ምክትል ከንቲባ